# ዜና ኢሕአፓ

ዴሞክራሲያዊ / Democratic

በኢሕአፓ የፖለቲካና የሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ
በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ የሚወጣ የዜና መጽሔት

ቅጽ 1፤ ቁጥር 2 — መጋቢት 2000 ዓ.ም.


## ርዕሰ አንቀጽ

### ወርኃ - የካቲት፣
### የሕዝባዊ ትግል ማቀጣጠያ
### የሰማዕታት መዘከሪያ

የካቲት ግም ሲል ቀድሞ ከፊታችን ድቅን የሚለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር ለእኩልነትና ለፍትሕ ሆ ብሎ በጋራ የተነሳበት የስልሳ ስድስቱ ሕዝባዊ አብዮት ነው:: ይሁን እንጂ ወርኃ-የካቲት ከዚህ ታላቅ ድል በፊትም አያሌ ሌሎች ድሎች የተመዘገቡበትም ነው፤ በተለይ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን::

የካቲት 23 1888 ዓ.ም. በተለይ ኢትዮጵያውያን ለራሳቸውም ለሌሎችም ጥቁር ሕዝቦች አርዓያነት ያለው እጅግ ታላቅ ድል ያስመዘገቡበት፤ ቅኝ ገዥዎችና ተባባሪዎቻቸውን የሽንፈት ማቅ ያከናነቡበት፤ የትናንቶቹ አያት ቅድመ-አያቶቻችን በጎሳ፣ በዕድሜ፣ በፆታ ወይም ሌሎች ምክንያቶች ሳይከፋፈሉ ለሃገራቸው ነፃነት ሲሉ በአንድነትና በጀግንነት ተዋግተው ሃገራቸውን ለመውረር ድንበር ተሻግሮ የመጣን ቅኝ ገዢ ድባቅ የመቱበትና ለዛሬው ትውልድ ነፃነቷንና አንድነቷን ጠብቃ የኖረች ክብርት እናት ኢትዮጵያን ያስረከቡበት ታሪካዊ ቀን ነው::

- ዕፁብ ድንቅ ፤ ታሪካዊ ዕለት::

የካቲትን ስናስብ ታድያ ሌሎችም አያሌ ታሪካዊ ክንዋኔዎችን አብረን እያስታወስን ነው:: ለአብነት ለመጥቀስ ያህል፤

1. ዓረቦችና ቱርኮች ባቀነባበሩት ሴራ ተደግፎ በጥፋት ላይ የተሰማራው የግራኝ መሐመድ ጦር ድል የተመታው በየካቲት ወር 1542 ዓ. ም. ነው::
2. አገራችንን በቅኝ ግዛትነት ለመቆጣጠር በሐረር በኩል የመጣው የፋሺስቱ ኢጣሊያ ጦር ድል የተመታው በየካቲት ወር 1896 ዓ. ም. ነበር::
3. ለረጅም ዓመታት በባርነት ቀንበር ስር ሲማቅቁ የኖሩት ጥቁር አሜሪካውያን ወገኖቻችን ለነጻነታቸዉ ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለው ለመጀመሪያ ጊዜ የተስፋ ጭላንጭል ያዩት በካቲት ወር 1960ዎቹ ነበር::

እነዚህና ሌሎችም ሊጠቀሱ ከሚገባቸው ወርኃ-የካቲት ካፈራቻቸው ታላላቅ ግብረ-ሰቦች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው::

የየካቲት አብዮት በአገራችን ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተንሰራፍቶ የኖረውን የፊውዳል ስርዓት ለአንዴና ለሁሌ ገርስሶ የጣለ ሕዝባዊ አመጽ ነው:: ለሕዝባዊው አመፁ መንስኤ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል:-

- ግብር ይቀነስልን ብለው

- የትግራይና የጎጃም እንዲሁም የሌሎች ክፍላተ-ሃገራት አርሶ አደሮች ያካሄዱት አመፅ፤
- ለሐገራቸው ዳር ድንበርና ለወገናቸው ነጻነት የተዋጉ አርበኞች ወደጎን ተገፍተው ለፋሽስት ኢጣሊያ ያደሩ ባንዳዎች መሾምና መሸለም እውነተኛ አርበኞችንና የአርበኞች ቤተሰቦችን በንጉሱ ላይ ከፍተኛ ቅሬታ እንዲያድርባቸው ማድረጉ፤
- መሬት ለዘውዳዊው አገዛዝ ታማኝ ለሆኑ ጥቂት ግለሰቦች በብዛት በመሰጠቱ ሰፊውን አርሶ አደር በጭሰኝነት ስር እንዲማቅቅ ማድረጉ፤
- ሕክምናና ትምህርት ለሰፊው አርሶ አደርና ሰርቶ አደር እንዲሁም ቤተሰቡ አለመዳረሱ፤
- የሁሉም ያገሪቱ ብሔር /ብሔረሰቦች የእኩልነት መብት አለመጠበቅና ይባስ ብሎም መነፈግ፤
- የሰብዓዊ መብቶች መጣስና መደፈር በተለይም በነፃነት የመናገር፣ የመፃፍ፣ ወዘተ፤ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ንጉሱና ሹማምንቶቻቸው ካልፈቀዱ በስተቀር መነፈጋቸው፤
- በነጻ የመደራጀት መብቶች የተከለከሉ መሆናቸው፤
- የመከላከያ ኃይሉ፣ በተለይም ደግሞ የጦር ኃይሎች፣ መብት አለመከበር፤ ከቤተሰቦቻቸዉ ተነጥለዉ ለረዥም ዓመታት ከቦታ ቦታ መንገላታት፤ ይባስ ብሎም ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን ሊመግብ የሚችል በቂ ደመወዝ አለማግኘት፤
- የፋብሪካዎችና የልዩ ልዩ ኩባንያ ሰራተኞች መብትና የኑሮ ሁኔታ አለመስተካከል፤
- በሰራተኛና በአሰሪ መካከል ቅጥ ያጣ የበላይና የበታች ወይም የጌታና ሎሌ ዓይነቱ አሠራር መስፋፋት፤
- በዚህም ምክንያት የዩኒቨርስቲና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች "ዳቦ ለተራበ" "መሬት ላራሹ" "ድርብ ጭቆና ይውደም" ና የመሳሰሉ መፈክሮችን ለማንገብ መገደድ፤ ብሎም ከታጠቀ ወታደር ጋር ፊት ለፊት ለመላተም መድፈር፤
- በነዳጅ ዋጋ መናር ምክንያት የባለ ታክሲዎች የሥራ ማቆም አድማ፤
- የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር የተማሪውን ጥያቄ በመደገፍ ለትግሉ እገዛ ማድረግ፤
- ከሁሉም በላይ ደግሞ በአገራችን ውስጥ በወቅቱ፤ በተለይም በወሎና በትግራይ የተከሰተውን አሰቃቂ ድርቅና የረሃብ አደጋ ንጉሡና ባለሚሎቻቸው ከህዝብና በዓለም ለመደበቅ ያደረጉት ጥረት፤
- ባጠቃላይ የዘውዱ ስርዓት ቁንጮ ሥልጣንን የሙጥኝ ማለትና ለለውጥ ጨርሶ ዝግጁ አለመሆን ለወርኃ-የካቲት ሕዝባዊ አብዮት መወለድ ዓይነተኛ ምክንያቶች ናቸው::

እንግዲህ እነዚህና ሌሎችም ተዳምረው የየካቲትን አብዮት ይውለዱ እንጂ ቀደም ሲልም በነጀኔራል መንግሥቱና ገርማሜ ንዋይ የተሞከረው የለውጥ ጥረት በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ መዝገብ ውስጥ ሊፋቅ በማይችል የወርቅ ቀለም ተዘግቦ የሚገኝ የሕዝባዊ ትግሉ አካል ነው::

የየካቲቱ አብዮት "ከሰማየ ሰማያት የወረደ" ተብሎ ይነገርለት የነበረውን ዘውዳዊ አገዛዝ ከስሩ ገርስሶ ቢጥልም ታድያ፤ ከዳር እስከዳር የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አብዮት ግን ብዙም ሳይቆይ በጣም ጥቂት በሆኑና ራሳቸውን ደርግ ብለው በሰየሙ ወታደሮች እጅ ገባ:: ለዚህ ሁኔታ መፈጠርም በወቅቱ የተደራጀ ሌላ የፖለቲካ ኃይል አለመኖሩም ከምክንያቶች አንዱ ነበር::

በመሣሪያውና በጡንቻው መናገር የሚቀድመው የጥቂቶች ወታደራዊ ደርግም የወቅቱን ተጨባጭ ሁኔታ ለጠባብ የሥልጣን ፍላጎቱ ለማዋል አልሞ ነበርና የሕዝቡን የፍትህና የነጻነት ጥማት በጥይት መለሰ፤: የሠፊውን ሕዝብ አብዮትም ቀለበሰ:: በሂደቱም እጅግ መጠነ ሰፊ የሆነ የሰው ሕይወት ጠፋ::
አፈናው ግድያው ተከተለ::

አለመታደልና “ታሪክ ራሱን ይደግማል” ሆነናም እስከዛሬ ድረስ ባገራችን ያለው ሁኔ ታ በዚያን ጊዜ ከነበረው ሁኔታ ጋር እጅግ በጣም ተመሳሳይነት ያለው የአፈናና የግድያ ዘመን በመሆኑ ሊፈታ ያልቻለ እንቆቅልሽ ሆኖ ህዝቡም "የፍትሓዊ አስተዳደር ያለህ" እያለ ድምፁን ከፍ አድርጎ ለማሰማት የተገደደበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን።
ይባስ ብሎም የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በከፋ መልኩ በተለየ መልክ እጅጉን መሰሪ በሆነ የጎሳ አስተዳደር ስር ወድቆ መገኘቱ የትናንትናውን የየካቲት ስልሳ ስድስት የአብሮነትና የአንድነት ትግል እንዲናፍቅና ብሎም፤ አንድ ሆኖ ባንድ ጎራ የሚያሰልፈውና በህዝቡ ልብ ውስጥ የገባ ጥርት ያለ ዓላማ ያለው ድርጅት አጣ እንጂ፤ ዳግም በጋራ ጠላት ላይ በጋራ የመነሳትን ብሔራዊ መርኅ ተግባራዊ እንዲያደርግ እያስገደደው ከመጣ ውሎ አድሯል።

እንደትናንቱ ሁሉ የዛሬውም ጎጠኛው የህወሓት አገዛዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰጥ ለጥ ረጥ አድርጎ ለመግዛት ወታደራዊ ኃይሉን አጠናክሮ የሚገኝበትና እንዳፈተተው የሚገዛበት የወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ነው የምንገኘው።
ዛሬም እንዳምናና ካቻምናው የሰፈው ህዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ አይደሉም። በወረቀት ላይ ብቻ የመፃፍ፣ የመናገር፣ የመደራጀት፣ ወዘተ፣ መብቶቹ የተጠበቁ መሆናቸው በግልጽ ቋንቋ ተቀምጠዋል። ነገር ግን የሚጽፉ፣ የሚናገሩና በነፃ ለመደራጀት የሚጥሩ ሁሉ በጠራራ ፀሐይ ባደባባይ ይደበደባሉ፤ ይ ታሠራሉ፤ ይገደላሉ፣ ባገር መኖር ያቃ ታቸውም ይሰደዳሉ። ከነፃ ድርጅቶች ይልቅ የእስር ቤቶች ቁጥር ይልቃል። አርሶ አደሩ ከፊውዳል ባላባቶች ጭሰኝነት ወደ መንግሥት ጭሰኝነት የተዘዋወረበት፤ የአገሪ ቱ የኢኮኖሚ አውታሮች በህወሓት አገዛዝ ባለስልጣኖችና ተከታዮቻቸው ሙሉ ቁ ጥጥር ስር የገቡበት ሁኔታ ነው ዛሬ በአገራችን ውስጥ ሰፍኖ የሚታየው ዕውነ ታ። የብሔር / ብሔረሰቦች መብት አገዛዙ በሚፈልገውና ለመቆጣጠርና እንዳሻውም ለመተርጎም በሚያመቸው መንገድ ብቻ ሆኖ የተገደበ፤ የመምህራን የጋዜጠኞች የተማሪዎችና ሌሎችም ዜጎች መብት የ ታፈነበትና እንዲያው በጥቅሉ አገርና ሕዝብ እግር ተወርች ተጠፍረው በህወሓትና በባለሚሎቹ ሙሉ ቁጥጥር ስር የዋሉበት ሁኔ ታ ነው ባገራችን የሚታየው። ወርኃ-የካቲት የትናንት የሃገር ጀግና ሰማዕታት መዘከሪያ የመሆኗን ያህል የሕዝባዊ ትግል ማቀጣጠያም ናትና ዳግም የወርኃ-የካቲትን ፈለግ እንከተል ዘንድ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) የትግል ጥሪውን ያቀርባል። ለተግባራዊነቱም በህዝባዊ ግምባሩ ፊት ለመሠለፍ ዝግጁነቱን ያረጋግጣል። በየካቲት ስልሳ ስድስት መባቻና ማግስት በኢሕአፓና በሌሎችም ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ደምና አጥንት የተቀጣጠለው የሕዝባዊ ትግል ዓላማ ከግቡ እስኪደርስ በጋራ ለጋራ እጅ ለእጅ ተያይዘን በሕብረት ትግል ደምቀን እንድንገኝ ጥሪያችን ነው። ወርኃ-የካቲት፤ የአድዋ ሰማዕታት መዘከሪያ ብቻ ሳትሆን የሕዝባዊ ትግል ማቀጣጠያና የጥቁር ህዝብም የነጻነት ቀን መታሰቢያ ናትና!

## ከዓለም አቀፍ ዜናዎችና ትግሎች ማኅደር

# ከሃገር ቤት

### ረሃብ ዳግም እንዣቦብናል፤ ህወሓት ግን የዕድገት አሃዝ ይቆጥራል።

ሰሞኑን ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በኢትዮጵያችን በቅርቡ ሊደርስ ስለሚችል የረሃብ አደጋ ጭንቀታቸውን በመግለፅ ላይ ናቸው።
በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ረኃብ ካንዣበበ ውሎ አድራል – እንደ ፖለቲካው ሁሉ ረኃቡም ከአገዛዙ ጭካኔ ጋር እየጨመረ መጥቷል። ወያኔ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ አንድም ዓመት ረኃብ የቀነሰበት ሁኔታ የለም።
ለጋሽ አገሮችም እርዳታ ከመስደድ አንድም ጊዜ አልቦዘኑም ። የኢትዮጵያ ታሪክ

በተደጋጋሚ የረሃብንም ታሪክ ያካተተ ነው፡፡ በ1999 ሰኔ ወር ላይ የብሪታኒያ የዜና ማዕከል እንደገለጸው 4.6 ሚሊዮን ህዝብ በ ረኃብ አደጋ ላይ መውደቁን ገልጾ ይህን አደጋ ለመከላከል 350000 ቶን እህል ማስፈለጉንና ይህ ካልተገኘ ግን ከፍተኛ ቁ ጥር ያለው ህዝብ እንደሚሞት ዘግቦ ነበር፡፡ ይህንም ዘገባውን በማጠናከር በአማራው ክልል በስተምዕራብ በኩል 2 ሚሊዮን፣ በደቡብ ምስራቅ የኦሮሚያ ክልል 900000፣ በትግራይ ክልል 80000 የሚሆን ህዝብ የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ በረኃብ በትር እየተቀጣ መሆኑንና ቀዬውን ጥሎ መሰደዱን ጠቁሞ ነበር፡፡ ከረኃቡ በተጨማሪ በሰሜኑ የሃገሪቱ ክፍል በተደረገዉ ጦርነት ከቦታው የተፈናቀለው 400000 ህዝብ ደግሞ በእርዳታ ብቻ ኑሮው ሊወሰን መገደዱን ገልጾ ነበር፡፡ ይህንን ችግር ለመቅ ረፍ የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች የሚችሉትን ሁሉ ሲያደርጉ በመንግስት በኩል ግን "እርዳታውን በገንዘብ መልክ በእጄ ካልሰጣችሁኝ ለእናንተ የፀጥታ ማስከበሪያ መንግስት ወጭ አያደርግም" እያለ ያለሐፍ ረት ሲያንገራግር ነበር - ህወሓት፡፡

ዛሬ ደግሞ እንደገና በሃገራችን የምስራቁ ክፍል ከፍተኛ የረኃብ አደጋ እየደረሰ መሆኑን የውጭ ታዛቢዎች ደጋግመው ሰሞኑን በሰፊው እየገለፁ ነው፡፡ በኦጋዴን ክልል ህወሓት የሱማሌ ነጻ አውጭ ነን ባዮች በሚያደርጉት ጦርነት ሳቢያ ገበሬው ምርት ማምረት ካለመቻሉ በተጨማሪ የዝናብ እጥረት ተዳምረው ሰፊውን ሕዝብ ከሞት አደጋ ላይ ጥለውታል፡፡ በጎዴ፣ በዋርዴር፣ በቆራሄ፣ በደገሃቡርና በፊቃ የተከሰተው ረኃብ አስከፊ መሆኑ ተዘግቧል፡፡ የእህል ዋጋ በጣም ከፍተኛ ደ ረጃ በመድረሱ ገበሬው የመግዛት አቅም የለውም፡፡ በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ከብት አርቢዎች አካባቢያቸውን እየለቀቁ ርቀው ለመሰደድ ተገደዋል፡፡ በተጨማሪ በአካባቢው ጸጥታ መናወጥ ምክንያት የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶችም አስፈለጊውን እርዳታ ለማድረስ መቸገራውን ገልጸዋል፡፡ መንግስት ተብየው ህወሓት ህዝብ በረኃብ እየረገፈ በማያገባው ገብቶ ድንበር ዘልሎ በሰው ሃገር ውስጥ ጦርነት ይቀፈቅፋል፣ በቀን ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ለጦርነቱ ያወጣል፡፡

ህወሓት ስልጣን እንደያዘ የደርግ መኳንንቶች በተድላና በደስታ ሲንፈላሰሱ ሰፊዉ ሕዝብ በረኃብ ሲረግፍ የሚያሳይ ፊልም አሰርቶ ይቀሰቅስ እንዳልነበር ዛሬ ራሱ በተመሳሳይ ድርጊት ለመዘፈቅ ችሏል፡፡ ይባስ ብሎ በሃገሪቱ ዉስጥ የኢኮኖሚ እድገቱ አስር ከመቶ ጨምሯል ሲልም ተደምጧል፡፡ ከዚህ ቀደም ረኃብ ሕዝቡን በሚጨርስበት ወቅት ምርታችን ተትረፍርፎ ለኬንያ ጭምር እርዳታ ለመስጠት ብቃት እንዳለው ሲያወራ ተደምጦ ነበር፡፡ ያይጥ ምስክር ድንቢጥ እንዲሉ የቀድሞው የአሜ ረካ ፕሬዘዳንት ካርተር ሳይቀሩ መጓጓዣ መንገድ የለም እንጅ ምርቱ በጎተራ ተት ረፍርፏል ብለው ነበር፡፡ ይሁን እንጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ በረኃብ መርግርፉ ዛሬም ድረስ አላቆመም፡፡ በተደጋጋሚ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በረኃብ አለንጋ መገረፍ አያሌ ምክንያቶች ሲደረደሩ ቆይተዋል፡፡

- የዝናብ እጥረት፣
- ገበሬው ማዕድኑ ባለቀ ወይም ባያሌ ለጠቀሜታ ከዋለ መሬት የሚያመርተው ምርት በቂ ባለመሆኑ፣
- መሬት በመንግስት እጅ በመሆኑ ገበሬው የራሱ ሳልሆነ መሬት እምብዛም እንክብካቤ ስለማያደርግ፣
- መንግስት ለገበሬው ትኩረት አለመስጠቱ፡፡ የዝናብ እጥረት እንደሚያጋጥም ሲታወቅም አስቀድሞ ዝግጅት አድርጎ ለመርዳት አለመቻሉ፣
- ገበሬው በዝናብ በሚበቅል እህል ምርት ብቻ በመወሰኑ፡፡ ወንዞችን ገድቦ በመስኖ ማርስን እንደልምድ አለማድረጉ፣
- ብዙ የመሬት ግብር በገበሬው ላይ መጫኑ፡፡ መንግስት ከፍተኛ ግብር በገበሬዉ ላይ ሲጥል ለመክፈል ያቃተው ገበሬ ያመረተውን ምርት ሸጦ ለግብር እያደረገ ቤተሰቡ ለ ረኃብ መጋለጡ፣

- የህወሓት አገዛዝ በንግድ ስራ በመሰማራቱ ገበሬውን በከፍተኛ ዋጋ እያንጓጓ ምርቱን እንዲሸጥ ማደፋፈሩና

ሌሎችም በምክንያትነት ሲደረደሩ ቢኖሩም የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም እንደአምናና ካቻምናው በህወሓት ጨቋኝ አገዛዝ ስር እየማቀቀ "ረሃቤ ጥማቴ እርዛኔ ሶስቱ፤ ይደበድቡኛል ባንድ እየዶለቱ" ከሚለው የትናንት የሰቆቃ ዝማሬው አልተገላገለም። (የዜና ኢሕአፓ ቃል አቀባይ፤ ከአዲስ አበባ)

# አረናና ህወሓት፤ እንድም ሁለትም፤

ህወሓት በቅርቡ "አንጃ በቀለብኝ" በሚሉ አዲስ አሉባልታ እጅጉን ተወጥሮ መገኘቱ በብዙ የሃገራችን የዜና አውታሮች ተደጋግሞ ተገልጿል። እንደሚታወቀው በ1993 ዓ. ም. የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ግምገማ ባደረገበት ወቅት በአመራሩ ውስጥ መከፋፈል መፈጠሩ የሚታወስ ነው። በተለይም የህወሓትን ትምክህተኝነት፣ ጠባብነት፣ በሰፈር ልጅ መተማመንና ቂመኝነት እንዲሁም በሃገሪቱ ሉዓላዊነት ጉዳይ ዙሪያ በተፈጠሩ ልዩነቶች ሳቢያ በአመራር አካሉ ዘንድ የግንኙነት መሻከር፤ ብሎም የአመለካከት ልዩነት መስፋት፤ ለጥቆም በህወሓት ኃይል ላይ ከፍተኛ ክፈተት ተፈጥሯል። በተጠቀሰው ጉባዔ ላይ ልዩነት ከተከሰተም በኋላ ህወሓት ራሱን ህወሓት ተሓድሶ በሚል ሊጠራ ሲገደድ በህወሓት የትግል ዓላማ መሳት ምክንያት ከድርጅቱ ለመለየት ተገደድን የሚሉት ደግሞ ራሳቸውን "አረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ሉዓላዊነት" በሚል ለቀጣይ ትግል ዝግጁነታቸውን ይፋ አድርገናል ብለዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሰሞኑን ህወሓት ተሓድሶ አረናንና ከዚህ ድርጅት ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው የሚላቸውን በተለይም የትግራይ ተወላጅ ኢትዮጵያውያን ዜጎች በመወንጀልና በተለይም ህወሓት የጀመረውን ዴሞክራሲያዊ ጎዳና ለማደናቀፍ የሚጥሩ፤ በ1993 ዓ. ም. በተደረገው ግምገማ ወቅት አንገመገምም ብለው ረግጠው የወጡ፤ ድርጅቱን የበተኑ፤ የሰማዕታት ጓዶቻቸውን ዓላማ በመዘንጋት የአባላትን ውሳኔ ጥሰው የተለዩ፤ ድርጅቱን የከዱና ለጠባብ ኃይሎች አሳልፈው የሰጡ፤ እንዲሁም እልሽኞችና ቀናተኞች ናቸው በሚል በሰፊው በመቀስቀስ ላይ ይገኛል።

ህወሓት ተሓድሶ በዚህም ሳይወሰን በቅርቡ በተለይ በትግራይ ክልል ላሰማራቸው ካድሬዎችና ተከታዮቹ የሚስጢር መመሪያ አውጥቶ አሰራጭቷል።

በዚህ በትግርኛ ቋንቋ በተፃፈ መመሪያ መሰረት የህወሓት ተሓድሶ ካድሬዎችና ተከታዮች አረና ለግል ስልጣን ጥቅም እንጂ ለሕዝብ እንዳልቆመ አጥብቀው ለሕዝብ እንዲያስረዱ ፤ የውጭ ኃይል ጥገኛ ቡድን እንደሆኑና ለሕዝብ ምንም የማይፈይዱ እንደሆኑ በሰፊው እንዲገለፁ፤ የአረና ዓላማ እንዳይሳካ ቀጥተኛም ሆነ ኢቀጥተኛ በሆነ መንገድ አበክረው እንዲታገሉ፤ ከሻዕቢያና ሌሎች ጠባብ ኃይሎች ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያላቸው ፀረ-ትግራይ ሕዝብ እንደሆኑ ማጋለጥ እንደሚገባቸውና አረናን በቁርጠኝነት ለመዋጋትም እንዲቻል ሕዝቡን እንዲያስታጥቁ በመጨረሻም ሕዝቡ ህወሓትን እንዲቀበል በአካባቢዎች የተጀመሩ የልማት እንቅስቃሴዎችን ማፋጠንና ተግባራዊ ማድረግ በዚህም ሳቢያ የሕዝቡን አመኔታ ለማግኘት መጣር እግረመንገድንም ከህወሓት በስተቀር ሕዝቡ ሌላ አማራጭ እንደሌለው በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እንዲወተውቱና እንዲቀሰቅሱ ጥብቅ ትዕዛዝ አስተላልፏል። የመመሪያው በስውር መሰራጨት እንደተደረሰበትም የአረና አመራር አባላት ከዚህ በፊት ከተለመደው ውጭ አደባባይ በመውጣት በልዩ ልዩ መገናኛ ብዙሃን መግለጫዎችና ቃለመጠይቆች በመስጠት ላይ ናቸው። በዚሁ መሰረት አቶ ገብሩ አስራት "ደሃይ ትግራይ" በሚል ርዕስ በአንድ በትግራይ ክልል ለሚታተምና ለሚሰራጭ መፅሄት ሰፊ ቃለመጠይቅ መስጠታቸው ሲታወቅ በቅርቡ ደግሞ ወይዘሮ አረጋሽ አዳነ ከሪፖርተር ጋዜጣ ጋር ስለአረና ዓላማና የወደፊት ዕቅድ ዝርዝር ቃለ-መጠይቅ ማድረጋቸው ታውቋል።

ወይዘሮ አረጋሽ ከህወሓት ተሓድሶ ለመለየት የተገደዱት ድርጅቱ ከዕለት ዕለት ዓላማውን እየሳተና ፍፁም አምባገነን እየሆነ በመቀጠሉ መሆኑን በመግለፅ ድርጅቱ በኤርትራ ጥያቄ ላይ የወሰደው ኢትዮጵያን እንደ ቅኝ ገዢ አድርጎ የመቀበል ታላቅ ስህተትና እንደሃገር ከተቆጠረችም በኋላ በመርህ ላይ የተመሰረተ ግልፅ መመሪያ አለመከተል እንዲሁም ኢትዮጵያን ያለባህር በር እንድትቀር ያደረገ ውሳኔ መቀበላችን በህወሓት ውስጥ ለተከሰተው መከፋፈል ዋነኛ ችግሮች ነበሩ ብለዋል:: አያይዘውም ህወሓት በጊዜው የተፈጠሩ ልዩነቶችን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመፍታት ፈቃደኛ ባለመሆኑና የአሁኖቹን የአረና አባሎችን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ድርጅቶችን ሳይቀር በጠላትነት የመፈረጅ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባራት ላይ በሰፊው የተሰማራ በመሆኑ ዛሬ ቁጥጥሟቋ ስር ባደረጋቸው መገናኛ ብዙሃን ዘዴዎቹ የአንድ ወገን የውንጀላና የስም ማጥፋት እንዲሁም የመከፋፈል ተግባር በህወሓት በሰፊው እየተፈፀመ መሆኑ ይበልጥ የትግራይንም ሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለትግል የሚያዘጋጅ ወቅት ላይ ደርሰናል ብለዋል::

ህወሓት በበኩሉ አረናን ለመታገል ካስተላለፈው ሚስጥራዊ መመሪያ በተጨማሪ ካድሬዎቹና ተከታዮቹ በመቀናጀትና በንዋይ ፍቅር ሊገኙ የሚችሉ ረዳቶችን በማከል፤ እንደየአካባቢው ሁኔታ የሚመጥን ዘዴ በመጠቀም የሕዝብ ንብረት የሆኑ የስልክ የፖስታና ሌሎችም ዘዴዎች በመጠቀም ፀረ-አረና ትግላቸውን እንዲያጧጥፉ ጥብቅ መመሪያ አስተላልፏል::

*(የዜና ኢሕአፓ ቃል አቀባይ፤ ከትግራይ)*

## ምርጫው ካሁኑ ተጨናግፏል፤ የተቃዋሚ ድርጅቶች ምሬት

በሃገራችን ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ምስረታ በሚደረገው ትግል ሂደት ገዢው ስርዓት የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ ዳግም እየበረታ መሂዱ የሚጠበቅ ቢሆንም ህወሓት በተለይ አዳዲስ ስልቶችን ፀመጠቀም በሃገር ቤት በሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ በሰፊው ቀጥሎበታል::

በተለይም ባሁኑ ወቅት በፓርላማ መቀመጫ ያላቸው የሚባሉትን ተቃዋሚ ድርጅቶች ጭምር እያዋከበ መሆኑ ብዙዎችን ያስገረመ ሲሆን በቅርቡ በደረሰን መረጃ መሰረት ኢዴፓን ያሳለፈውን የጋራ ውሳኔ በመጣስ ከግንቦት 97 ማግስት በተናጠል ወደፓርላማ የገቡት ዶክተር በየነና ዶክተር መራራ ከፍተኛ እሮሮ ሲያሰሙ መደመጣቸው ብዙዎችን እያስገረመ ነው:: እንደሚታወቀው ህወሓት በሃገራችን በሶስት የተለያዩ ጊዜያት ምርጫዎች እንዲካሄዱ ቢያደርግም በሁሉም ምርጫዎች በራሱ የምርጫ ቦርድ ምርጫ አስፈፃሚ አካልና ፍርድ ቤቶች በመታገዝ የስልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ተጠቀመባቸው እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳች የፈየደው ነገር የለም::

ባሁኑ ወቅት ህወሓት ለሚያዝያ 2000 ዓ. ም. ያካባቢና ማሟያ ምርጫ ተዘጋጁ እያለ ሕዝቡንና ተወዳዳሪ ድርጅቶችን በማጣደፍ ላይ ሲሆን በራሱም በኩል ባዲስ አበባ ብቻ ከሰላሳ ሺህ በላይ እጩዎችን እንዳዘጋጀ ይፋ አድርጓል:: የሚያዝያውን ምርጫ ልዩ ከሚያደርጉት አንዱ ከሶስት መቶ በላይ እጩዎች ባንድ ቀበሌ እንዳይሳተፉ አገዛዙ ማዕቀብ ማድረጉ ሲሆን ይህም የተለመደ የአገዛዙ የማጭበርበሪያ ዘዴ መሆኑ ለብዙዎች ግልፅ ከሆነ ሰንብቷል:: ከዚህም በተጨማሪ እንደከዚህ በፊቱ ሁሉ በነዋሪዎች ላይ የግብር ዋጋ በመጨመር ህወሓት በማስፈራራቱና በማዋከቡ በስፋት እንደቀጠለ ሲሆን አዲሱ ክስተት ደግሞ ፖሊስ ጣቢያዎችና የህወሓት ባለስልጣኖች መኖሪያዎች ሳይቀሩ ለምርጫ ጣቢያነት መታጨታቸው ነው:: ባሁኑ ጊዜ ሕዝቡም ሆነ ተቃዋሚ ድርጅቶች የሚያዝያው ምርጫ የተለመደው ማጭበርበር የሚታይበት ለመሆኑ ሙሉ እምነታቸውን እየገለፁ ሲሆን ነፃ ምርጫና ነፃ አስመራጭ ቦርድ በሌለበትና ሁሉም ነገር በህወሓት ኢሕአዴግ ቁጥጥር ስር በሆነበት ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚያሸጋግር

የምርጫ ስርዓት በመጪው ሚያዝያ እንደማይካሄድ የታዛቢዎች ሁሉ ግምት ሲሆን ሕዝቡ በተቃዋሚ ድርጅቶች በኩል ሊደረግ የሚችልን የጋራ ጥረት አሁንም በጉጉት በመጠባበቅ ላይ ነው::

*(የዜና ኢሕአፓ ቃል አቀባይ፤ ከአዲስ አበባ)*

# ከውጭ ሃገር

## ምርጫና መዘዙ በኬንያ

ሰላሳ ሰባት ሚሊዮን ዜጋ በሚኖርባት ኬንያ ባለፈው ዓመት መጨረሻ የተደረገዉ ምርጫ ዛሬም ሁለት ወር ካለፈው በኋላ መዘዙ አላለቀም::

የኬንያውን የ2007 ምርጫ ባገራችን ከተደረገው የ2005 ምርጫ ከተለያዩ መመዘኛዎች አኳያ ማወዳደሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል::

በኬንያ ሁለቱ ዋነኛ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በመንግስት በኩል "ብሔራዊ ህብረት ፓርቲ" የተባለው በስልጣን ላይ ያለው በፕሬዘዳንት ኪባኪ የሚመራው ባንድ በኩልና በተቃዋሚዎች በኩል ደግሞ "ብርቱካን ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ" የተባለዉ በኦዲንጋ የሚመራውና ምርጫው ተጭበርብሯል ብሎ ተቃውሞ ያቀረበው ተቃዋሚ ፓርቲ ናቸው::

እንደ አገራችን ሁሉ በኬንያም በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የሰየመው የምርጫ ኮሚሽን ሲኖር፣ ከኛ የሚለይበት ጉዳይ ቢኖር ከዚህ ቀደም በ2002ና በ2005 ያካሄዳቸው ምርጫዎች በመዛኙ ፍትሃዊ ነበሩ ተብሎ መታመኑ ነው:: ከ22 የኮሚሽን አባላት 17ቱ በኪባኪ በቅርቡ የተሾሙ ነበሩ:: ባገራችን እንደተደረገው በቅድመ ምርጫ አስመራጭ ኮሚሽኑ ይለወጥ የሚል መፈክርም አልተሰማም:: ከምርጫው በፊት ልክ ባገራችን እንደተደረገው የምርጫ ታዛቢዎች ከምዕራቡ ዓለም ወደ ኬንያ ገብተው ነበር:: ከኛ በሚለይ ሁኔታ ግን 17 ሺህ ያህል ከተለያዩ የሲቪል ማህበረሰቦች የተውጣጡ ያገሪቱ ዜጎች በምርጫ ታዛቢነት ተሰማርተው ነበር:: እንደ ሚታወሰው ባገራችን ተደጋግሞ የራሳችን ዜጎች የሆኑ ታዛቢዎች መንግስትን ምርጫ ለመታዘብ ፈቃድ ጠይቀው በመከልከላቸው፤ በመጨረሻ ወደ ፍርድ ቤት ሂደው ፈቃድ ቢያገኙም ፈቃዱ ዘግይቶ በመድረሱ ኢትዮጵያዊ ዜጎች በታዛቢነት አልተሳተፉም::

እንደ አገራችን ምርጫ በኬንያም ከርዕሰ-ብሄር ምርጫ በተጨማሪ የፓርላማ አባሎችና ያካባቢ ወኪሎች ምርጫ ተደርጓል:: ወደ 10 ሚሊዮን ያህል መራጭ በኬንያው ምርጫ እንደተሳተፈም ይነገራል::

ችግሩ የጀመረው ልክ እንደ አገራችን የምርጫው ዉጤት ሲነገርና ከዚሁ ውጤት ጋር በተዛማጅነት በተያያዙ ጉዳዮች ዙሪያ ነዉ:: አንዱ የዉጤት መመዘኛ ድምፅ የሰጡ ሰዎችን ውጭ ጠብቆ ለማን ድምፅ እንደሰጡ በመጠየቅ ይህን አሃዝ በመጠቀም የሚደረግ ግምት ነዉ:: "ዓለም አቀፍ ሪፖብሊካን ተቋም" የሚባለው አሜሪካዊ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ባደረገው ድምፅ ቆጠራ ተቃዋሚ ፓርቲው 8 በመቶ እንዳሸነፈ ዘግቦ ነበር:: እንደሚታወሰው ይህ ተቋም የኢትዮጵያን ምርጫ ለመታዘብና በምርጫ የሚሳተፉ ዕጩዎችን ለማሰልጠን ሲዘጋጅ የኢሕአዴግ አገዛዝ አገር ለቅቆ እንዲወጣ ነው የተደረገው::

በተጨማሪም የተቃዋሚው ፓርቲ አባሎች በፓርላማ ምርጫ የኪባኪን ፓርቲ በእጥፍ ያህል ነው እንዳሸነፉ ተጠቁሟል:: ይሁን እንጂ የመጀመሪያው ችግር የተከሰተው የምርጫው ውጤት የሚነገርበት ጊዜ 1 ቀን በመዘግየቱ፤ በቋፍ ላይ የነበሩት ዜጎች የመደናገጥና ድምፃችን ሊሰረቅ ይችላል የሚል ጥርጣሬ አደረባቸው:: ያካባቢ ዉጤቶች ተቃዋሚ ፓርቲውና መሪው ኦዲንጋ እየመሩ የነበሩ መሆናቸውም ይበልጥ ጥርጣሬውን አጠናከረው::

እንደሚታወሰው ባገራችን የመጀመሪያ የአደጋ ምልክቶች ገና ቆጠራው ሳይጠናቀቅና የተቆጠረው ማረጋገጫ ሳያገኝ ኢሕአዴግ ማሸነፉን መግለፁና አስከትሎም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጁ ነበሩ።

እንደተፈራው በኬንያም ልክ በኢትዮጵያ እንደተደረገው የምርጫ ኮሚሽኑ በስልጣን ላይ ያለው የኪባኪ መንግስት በ2 ከመቶ ማለትም በ231728 ድምፅ የበላይነት አግኝቶ ማሸነፉን ይፋ አደረገ።

የአይን ምስክሮች ያዩዋቸው ዓይን ያወጡ ቅጥፈቶች ስለነበሩ የኬንያን ህዝብ በእጅጉ የአሳዘነ ክስተት ሆነ። ለምሳሌ የኮሚሽኑ ሊቀመንበር ከኪባኪ ወረዳ የመጣ ድምፅ ስሌት 115 ከመቶ ማለቱ ግልፅ ማጭበርበር እንደሆነ እያወቀ፣ 85 ከመቶ ብላቸሁ ለውጡ ብሎ ታዛቢዎች ባሉበት ማሳለፉ በኮሚሽኑ ስራ ላይ ህዝቡ እምነት እንዳይኖረዉ ታላቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። ከአፈርኩ አይመልሰኝ ሆነና የምርጫው ኮሚሽን በዚሁ በሌብነት ስራ በመቀጠል ልክ እንደ ኢትዮጵያዊ አቻው በተከታታይ የሚከተሉትን ወንጀሎችና ግፎች ፈፀመ።

- የማስረጃ ድጋፍ የሌላቸው የምርጫ ውጤቶች መቅረብ ጀመሩ።
- የፓርቲ ሃላፊዎችና ወኪሎች ያልፈረሙባቸዉ የምርጫ ውጤቶች ተላለፉ።
- የፎቶ ኮፒ ቅጅዎችና የሃሰት ሰነዶች እንደማስረጃ ተቀባይነት አገኙ።
- ስማቸው በ ኦ የሚጀምረዉ የተቃዋሚ ፓርቲው መሪ የኦዲንጋ ማህበረሰቦች የሆኑት የሉዎ ብሄረሰብ አባሎች የድምፅ መስጫ ወረቀትና የምርጫ ኮረጆ እንዳለ በሚያሰገርም አኳኋን ተሰረቀ።
- በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ለፓርላማና ላካባቢ ወኪሎች የሰጡት ድምፅም ጠፋ።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በኢትዮጵያና በኬንያ ብቻ ሳይወሰን ባብዛኛዉ የሶስተኛ ዓለም ሃገሮች የታህታይ ወዋቅር (ኢንፍራስትራክቸር) ችግሮች በምርጫ ሂደት ወቅት ከፍተኛ መሰናክል ይፈጥራሉ። እነዚህም ችግሮች የምርጫ ጣቢያዎች በሰዓቱ አለመከፈት፣ የተመደቡ ሰራተኞች ተሟላተው አለመገኘት፣ የሰነድ አያያዝ ችግርና ዜጎችን ካንድ ጣቢያ ወደ ሌላ ጣቢያ ማንገላታትን የመሳሰሉ ችግሮች ይከሰታሉ።

በኬንያ የምርጫውን መጭበርበር በመቃወም በተቃዋሚው በኩል የተወሰዱት እርምጃዎች በኢትዮጵያ ቅንጅትና ህብረት የወሰዷቸዉን እርምጃዎች ይመስላሉ። ሰላማዊ ሰልፎች፣ መንግስት ጉዳዩን በሰላም እንዲጨርስ መወትወት፣ ስራ ማቆም አድማና የመንግስት ንግድ ተቋማት ላይ ያነጣጠሩ አድማዎች መም ታትን የመሳሰሉ ይገኙባቸዋል።

በኬንያ ፍጥጫ ግን መሰረታዊ ልዩነት ባለው መልኩ ከኢትዮጵያው ፍጥጫ በተለየ የጎሳ ጦርነትን በጋበዘ መልኩ አስከፊ በሆነ ሁኔ ታ ብዙ ንፁሃን ዜጎች ህይወታቸውን ለማጣት በቅተዋል። እስከ 1000 የሞቱ እንዳሉ ሲገመት፣ እስከ 250000 የሚሆኑ ከኑሯቸው ተፈናቃይ ሆነዋል።

## የኬንያ የምርጫ ውዝግብ ለምን ወደ ጎሳ ግጭት

ጉዳዩ ካገሪቱ ታሪካዊ ሁኔታዎችና ከፖለቲካ ፓርቲዎቹ አመሰራረት ጋር ይያያዛል። አገሪቱ ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነፃ ስትወጣ "ማው ማው" በተባለው የነፃ አውጭ እንቅስቃሴ በትጋትና በብዛት የተሳተፉት ኪኩዩ የተባለው ጎሳ አባላት ሲሆኑ እንግሊዞች ለቅቀው ከወጡ በኋላ እነሱ ይዘውት የነበረውን ለም መሬት፣ የፖለቲካ ስልጣን ወዘተ ጥቅሞች ለማግኘት ችለዋል። ለም መሬቱ በፊት በእንግሊዞች የተወሰደው ከአናሳ ጎሳዎች ስለነበረ

በኪኩዩዎቹና በሌሎቹ መካከል ቅሬታን የቋጠረ ታሪካዊ ሁኔታን ፈጥሯል:: ይህም የኪኩዩ ጎሳ አባል የሆነው ኪባኪ የምርጫ ተወዳዳሪ ሆኖ ምርጫው መሰረቁ ሁኔታውን አባባሰው::

በኢትዮጵያም በኢሕአዴግ በኩል የምርጫው ውጤት ወደ ውዝግብ መቀየር ወደ ጎሳ ጦርነት ሊያስወስድ የሚችል ርካሽ ፕሮፖጋንዳ ፈጥሮ እንደነበር የሚታወስ ነው:: የመለስንና የበረከትን ኢንተርሃምዌ የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ልብ ይሏል::

የኬንያና የኢትዮጵያ የምርጫ ውዝግብ ሌላም ዓቢይ ልዩነት አለው:: ይኸውም የውጭ ሃይሎች በወቅቱ በወሰዱት አቋዋም ላይ ነው:: የምርጫ ታዛቢዎቹ ከሞላ ጎደል በመንግስታቱ በኩል የተፈፀመውን ማጭበርበር አውግዘዋል:: ልዩነቱ ውዝግቡን ለመፍታት በተደረገውና በሚደረገው ጥረት ላይ ነው:: ይህ ደግሞ ምዕራባውያንን ብቻ ሳይሆን አፍሪካውያንንም ይጨምራል:: የአፍሪካ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ኢትዮጵያ ውስጥ አሳፋሪ ምስክርነት መስጠታቸዉ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነዉ::

በኬንያ ጉዳይ በሽምጋይነት በመጀመሪያ አፍሪካውያን ግምባር ቀደም ሚና መጫወታቸው የሚያኮራ ነው:: የአፍሪካ ህብረት፣ የደቡብ አፍሪካው ካህን ዴዝሞንድ ቱቱ፣ የጋናው ፕሬዚደንት ኩፉርና የቀድሞው የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሃፊ አናን በኬንያ መንግስትና በተቃዋሚው ፓርቲ መካከል ሰላም ለማምጣት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል:: ተቃዋሚ ፓርቲውም ዓለም አቀፍ ድጋፍና እውቅና በማግኘቱ የመደራደሪያ ስልቱን ከፍ በማድረግ የጋርዮሽ መንግስት እንኳን አልቀበልም ብሎ ነበር - ለጊዜው ::

አፍሪካውያንም ሆኑ ምዕራባውያን በኬንያ የሰላም መስፈን ጉዳይ ላይ ይህን ያህል መ ረባረብ ያደረጉት ኬንያ ካላት በጎ ስምና ታሪካዊ ዝና ይመስላል:: እንደ ሶማሊያ በጦርነት ዋዥቃ አፍሪካን አታስደብም፣ እንደ ኢትዮጵያ ረሃብተኛ ሆና ክፍለ ዓለሙን አታስወቅስም፣ እንደ ሱዳን በዜጎቹዋ ላይ ዘግናኝ ጭፍጨፋ አታደርግም:: ስለዚህ ምንም እንኳን በጉቦና በሙሰኝነት የከፋ ታሪክ ቢኖራትም ደልዳላና የቱሪስት መስህብ አገር በመሆንዋ እድለኛ ከሆነች ኬንያ ይህን አስቀያሚ ሁኔታ ወደ ወርቃማ ዕድል በመለወጥ የዴሞክራሲ ጎዳናን የምትያያዝበት ታሪካዊ ጊዜ እንዲፈጠርላት የሰላም ወዳድ ሕዝቦች ሁሉ ምኞት ነው::

*(የዜና ኢሕአፓ ቃል አቀባይ፣ ከኬንያ)*

# ከታሪክ ማኅደር

## አድዋ በታሪክ ፀሐፊዎች ብዕር

“……የውስጥ አንድነታችን ባፄ ቴዎድሮስና ባፄ ዮሃንስ ሃይልና ድካም ከተደላደለ በሁዋላ፣ አፄ ምኒልክ ደግሞ በፋንታቸዉ ሃይሉን በትእግስትና በሰላም ስለ አጠናከሩት የአድዋ እለት ጣልያንና ምእራባዉያን ባልጠበቁት መንገድ የኢትዮጵያ ህዝብ ከነመሳፍንቱ ባንድ እግር ቆሞና ባንድ የስልጣን መስመር ተሰልፎ ወራሪ ጠላቱን መለሰ:: ከዚህም በሁዋላ ምእራባውያን ኢትዮጵያ ህብረትም የፀና መንግስት አቀዋምም እንዳላት ተገነዘቡ:: ከዚህ ግንዛቤም በሁዋላ ኢጣልያንና የቀሩትም የአውሮጳ ሃያላን የወረራውን ስሜት ሰርዘው ሌጋሲዮን በመክፈት ወኪል ማስቀመጥና ወሰን መካለልንም ጀመሩ::….” *ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ አፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት፣1990 ዓ. ም.*

"…There are three reasons why we commonly refer to some happening as a historic event - either it occurs for the first time; it has significant consequences; or it is symbolically important. As a first time event, Emperor Menelik’s cession of the Bogos highlands to Italy in 1889 has been described as historic, as the first time that an Ethiopian ruler ever voluntarily ceded territory to a foreign power. In the same vein, Abebe Bikila’s victory in the marathon race in the 1960 Olympics at Rome was historic, as the first time that an an Ethiopian won a gold medal………..." ***(Donald N. Levine, The Battle of Adwa As "Histiric" Event, 19..., page 1)***

# ከዴሞክራሲያ ማኅደር

“...ከአድዋ ድል በኋላ አፄ ምኒልክ በድል አድራጊነት ወደ ዋና ከተማው አዲስ አበባ ገብተው ከኢጣልያ መንግስት ጋር የመጨረሻ ውል ከተፈራረሙ በኋላ ንጉሰ ነገስቱና ሚኒስትሮች ያተኮሩት የአውሮጳን ስልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ አስገብተው የልማት ስራ ማስፋፋቱ ላይ ነው:: በአውሮጳ እነሚካኤል ፋራዳይ የብርሃን ዘዴና ጉልበት፤ እነአሌክሳንድር ግራሃምቤል በቴሌፎን መነጋገርን አግኝተው፤ ሌላውም ውኃን ከወንዝና ከምንጭ በቧምቧ እየጠለፈ ወደ ቤት ውስጥ በማስገባትና ወደ እርሻ ቦታ በመውሰድ ሰብላቸዉን ሲያለሙ፤ የህክምና፤ የኢንዱስትሪ፤ የሜካኒክ ስራ በየመልኩ እየተሻሻለ ሲሄድ ኢትዮጵያ በጥንቱ ኋላ ቀር መሳሪያ መጠቀሟን ትታ ወደ ዘመናዊ ዘመን በአስቸኳይ እንድትገባ የአድዋ ጦርነት በድል መጠናቀቅ ምክንያት ሆኗል...” ጳውሎስ ኞኞ፤ አፄ ምኒልክ፤ ሁለተኛ ዕትም፤ 1990 ዓ.ም.

"...March 1, 1896 Ethiopia defeated the Italian colonial army in the battle of Adwa. The victory signaled the decline of European colonialism in Black Africa..." The Encyclopedia Britannica, 15th Edition, 1996 Encyclopedia Britannica Inc.)

"...የዐድዋን ጦርነትና ከዚያም በፊት የተደረጉትን ውጊያዎች ከፍተኛ ነጥቦች የያዙ ጉዳዮች ነበሩባቸው:: ቁጥራቸው 20000 የሚሆን የሠለጠኑ የአውሮጳ ወታደሮች ካልሠለጠኑ ከአፍሪካ ወታደሮች ጋር ገጥመው በመደምሰሳቸው በዓለም ታሪክ ውስጥ የሌለ ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ በመድረሱ የሚያስደንቅ ሆነ:: ጦርነቱን አሰደናቂና አስገራሚ ያደረገው የሞቱትና የቆሰሉት ሰዎች ብዛት ብቻ አይደለም:: የጦርነቱ ውጤት ለቅኝ ገዢዎች ለወደፊት የሚገጥማቸውን ችግር የሚያመለክት አሳሳቢ ዜና መሆኑም ጭምር ነው:: የዚህ ጦርነት ውጤት በአፍሪቃ አህጉር ውስጥ ሌላ ኃይል መነሳቱን ያረጋግጣል:: የአህጉሩ ተወላጆችም አንድ ቀን በጦር ኃይል የመጠቀም ችሎታ እንደሚኖራቸው በመገመት ብርቱ ጥናትና ጥንቃቄ እንዲደረግ፤ የጨለማው አህጉር ተብሎ የሚጠራው ክፍለ ዓለም በአውሮጳውያን ላይ ያሳየው የመጀመሪያ እንቅስቃሴ የሚያሳስብ ሆነ::..." *ጆርጅ ኤፍ ኤች በርክሌይ፣ የዐድዋ ዘመቻና የአፄ ምኒሊክ አነሣሥ፣ 1979 ዓ. ም. (ትርጉም በዳኛው ወልደ ሥላሴ)*

"... ዛሬ የኢትዮጵያን ሕዝብ ስቃይና መከራ መልሶ መዘርዘር ሳይሆን ከግፍና ከመከራ ማዕበል የመውጫውን ብልሃት ማመንጨትና መተግበር ላይ ማትኮር በተለይም በፖለቲካ ትግል ተመክሮ ካላቸው እንደኢሕአፓ ካሉ አንጋፋ የፖለቲካ ድርጅቶች ብዙ የሚጠበቅበት ወሳኝ ወቅት ላይ ነን:: ጊዜው ኢሕአፓም ሆነ ሌሎች የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች ምን ማድረግና ማከናወን እንዳለባቸው ራሳቸውን መልሰው በዝርዝርና በጥልቀት መመርመር ግድ የሆነበት፣ ከዚህም በኋላ አማራጭ በማይገኝለት በሕብረት ትግል አረመኔውን አምባገነኑንና ዘረኛውን የሕወኃት መንግስት አሽቀንጥሮ በመጣል በግንቦት ሰባት 1997 ማግስት በአደባባይ የተሰረቀውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ድምፅ ማስመለስና ሕዝቡን ለአስተማማኝ ድል ማብቃት የግድ የሆነበት ነው::..." <u>ከዴሞ፣ ኢሕአፓና የኢትዮጵያ አንድነት ጥያቄ፣ ግንቦት 1994 ዓ.ም. ልዩ ዕትም፣ የተቀነጨበ::</u>

"...የጦርነቱ መንስዔ ወይም ምክንያት ባድመ በማን ግዛት ስር መሆን እንዳለባት ለማስረገጥ ነው የሚለው የሁለቱም ታሪክ በራዦች ጩኸት ሕዝብን ለማደናገር የተቀመረ የሀሰት ፕሮፖጋንዳ መሆኑ ከተረጋገጠ ቆይቷል:: ትናንት ከትናንት በስቲያ "ኤርትራ የምትባል አገር አለችና ነጻነቷን ቶሎ እወቁልኝ" ብሎ የተባበሩት መንግስታትና የአፍሪቃ አንድነት ድርጅቶችን ወጥሮ ኢትዮጵያን ያለምንም የባህር መውጫ በር ታፍና እንድትቀር ያደረገው ህወሓት እውን ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር ተቆጭቶ በጠላቶቿ ላይ ሊዘምት ነው ብሎ ለማመንም ግብሩና ምክሩ ዱባና ቅል ነውና ከቶውንም ተአማኒነት የለውም:: ሻዕቢያም ቢሆን በትብብር በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ፈጅቶ ከወታደራዊው መንግስት እጅ ፈልቅቆ የወደፊቱን ትውልድ ሳይቀር በሚጎዳ መልኩ የኤርትራን ክፍለ ሃገር ያስረከበውን ህወሓት በቁራሽ መሬት

ላብ አደሩና ፓርቲ ዓላማ ምንድነው? ባጭሩ ጭቆናን ማጥፋት ነው:: የከበርቴው መደብ ትርፍ ከማካበት በስተቀር ሌላ ዓላማ ስለሌለው ላብ አደሩ በትግሉ ይህን ከበርቴ፣ አቀባባይ ይሁን ሌላ ከስልጣን አሽቀንጥሮ መጣል አለበት:: መንግስት ደግሞ ከመካከል ላይ የቆመ ዳኛ ሳይሆን ገዱፊና ጨቋኝ መደቦችን ጥቅም የሚያስከብር በመሆኑ በላባደር መንግስት መቀየር አለበት ይላል:: በማርክሲዝም አመለካከት ራሱ የላባደር መንግስትም ቢሆን አንዴ ከመጣ በኋላ ቋሚነት የለውም:: የመደቦች ልዩነት ሲጠፋ ራሱ መንግስትም ይከስማል በማለት ማርክሲዝም ምኞቱን ሰማይ ላይ በማድረስ የአማኙን ልብ አነሁልሏል::

ማርክሲዝም በሃያልነቱ የዓለምን 1/3ኛ የመሬት ገፅ በቁጥጥር ስር አድርጎ ነበር:: በ1989 ከመውደቁ በፊት በሕይወት በነበ ረባቸው 60 ያሕል ዓመታት ያሰማቸውና ያጠፋቸው ጉዳዮች ዛሬም በታሪክ አዋቂዎች መካካስል ክርክር እንዳስነሳ ነው::

በልማት በኩል ሊጠቀሱ ከሚገባቸው የሶቭየት ሕብረትን ከነበረችበት ሁዋላ ቀር ፊውዳላዊ አገዛዝ አውጥቶ በኢንዱስትሪ የሰለጠነችና እንዲያውም ሃያል መንግስት እንድትሆን ያስቻለ ሰዕት ሊመሰረት መቻሉ በበጎ መታየት አለበት:: በመሆኑም የፋሺ ዝምና የናዚዝም አደጋ በዓለም ላይ ባንሰራራበት ወቅትና ሂትለር አውሮጳን እየተቆጣጠረ በሚገሰግስበት ወቅት ያንን አደጋ በመቋቋምና ሂትለርን በማሸነፍ ሶቭየት ሕብረት ታላቅ አስተዋፅዖ አድርጋለች:: ቀጥሎም ቻይና ዛሬ ወደሃያል መንግስትነት እንድታንሰራራ የረዳትን መሰ ረት የጣለ የማርክሲዝም ርዕዮት ነው ማለት ማጋነን አይደለም:: በተጨማሪም ማርክሲዝም ሁሌም በጦር ብቻ ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ ስልጣን ለመውሰድም እንደሚቻል ያሳየበት ሁኔታም በበጎ መ ታየት አለበት:: ይኸውም በቺሌ በሳልቫዶር አየንዴ መሪነት ኮምኒስቶች በሰላማዊ የስልጣን ውድድር የቀኝ ፓርቲዎችን በድምፅ ብልጫ አሸንፈው ከ1970-1973 በስልጣን ከቆዩ በኋላ በአሜሪካ አጋዥነትና በጥባጭነት አየንዴ ተገድሎ እነፒኖሼ ወደ ስልጣን መጥተዋል(ታሪክ አንዳንዴ ደግ ውና ፒኖሼም በሰፈረው ቁና የተሰፈረበትን ሁኔ ታ ለማየት በቅተናል):: ባጠቃላይ ከዚህ በፊት በጭቆና አፋቸው የተለጎመ የሕብ ረተሰብ ክፍሎች ለመብታቸው እንዲነሱና እንዲታገሉ፣ ለሴቶች፣ ለጭቁን ብሔሮች፣ ለቅኝ ግዛቶች፣ ለአናሳ የሕበረተሰብ ክፍሎች ማርክሲዝም ብርሃን አብርቷል ቢባል የማይገባውን መስጠት አይሆንም:: በተለይ ደግሞ ሶቭየት ሕብረት ለነፃነት ታጋዮች ያደረገችውን የማቴሪያል፣ የሞራልና የዲፕሎማሲ ድጋፍ ጨርሶ ሊረሳ አይገባም::

በሌላ በኩል ግን ማርክሲዝም መሰረታዊ ኃጢያቶችንና ግድፈቶችንም በውስጡ በመጸከሙና በመፈፀሙ ዞሮ ዞሮ የማታ የማ ታ ለራሱም መውደቂያ ምክንያቶች ሆነዋል:: ታላቁና መሰረታዊ ግድፈቱም የዲሞክራሲን ፅንሰ ሃሳብ ማውገርገሩ ነው:: ማርክሲዝም ዴሞክራሲን እንደማንኛውም ጉዳይ ከመደብ አንፃር ያየዋል:: ዛሬ በዓለም ላይ ተቀባይነት ያለውን የዴሞክራሲ ሃሳብ የቡርዣ(የከበርቴ) ዴሞክራሲ ይለዋል:: ማርክሲዝም የሚቀበለውና የሚፈቅደው የላብ አደሩ ዴሞክራሲ የሚለውን ነው:: ይህም ላባደሩን ወክሏል የተባለው የላብ አደር ፓርቲ የሚያደርገውን አምባገነንነት የሚያጠይቅ በሕብረተሰቡ ውስጥ ላሉት ሌሎች መደቦች (የላብ አደሩ አጋር ናቸው ተብለው ከተመሰከረላቸው ውጭ) መሰ ረታዊ መብታቸውን የሚሽር የናጠጠና ዓይን ያወጣ አምባገነንነት ነው:: በስሙም ስንትና ስንት ግፍና ወንጀል ተፈፅሟል::

የማርክሲዝም የላብ አደራዊ አምባገነንነት ፅንሰ-ሃሳብ በውስጡ በቅራኔ የተሞላ ስለሆነ የመብት መነፈጉ ጉዳይ ለከበርቴ አባሎች ብቻ ሳይሆን፣ ቀስ በቀስ የላብ አደሩ አባሎች ራሳቸው የሚጨፈጨፉበትና በመጨረሻ አንድ ፈላጭ ቆራጭ አምባገነን የፈለገውን ያለምንም ማስረጃ ወደሚገድልበትና ወደሚያጠፋበት የጨለማ ስርዓት የሄደ አስቀያሚ የታሪክ ክስተት ለመሆንም በቅቷል::

ማርክሲዝም ከናቀው፣ ዝቅ አድርጎ ሚያየውና የቡርዣ ዴሞክራሲ ብሎ ከሚጠራው አስተሳሰብ እንኳ በመብት አጠባበቅ በኩል ሊስተካከል አልቻለም::

የቡርዣ ዴሞክራሲ የተባለው የግለሰብ ዜጋ መብትን የመናገር የመጻፍ የመሰብሰብ የመደራጀት ወዘተ መብት ባመዛኙ ይቀበላል፣ ይተገብራል። የሰው ልጅ ሃይማኖትን ግን አበሻቅጧል፣ የምዕመናን መብንትም ረግጧል። ምዕራባዊ ዴሞክራሲ ስለሰው ሕይወት ክቡርነት ቢያንስ በወረቀት ደረጃ አለበለዚያም በከፊል ያወድሳል፣ ተግባራዊም ያደርጋል።

ማርክሲዝም ስለሰው ልጅ መጨቆን ማቆምና ስለመደብ አልባ ሕብረተሰብ እያወራ፣ የመንግስትን የጭቆናና የማፈኛ መሳሪያዎች አጠናክሯል። የማርክሲዝምን ጭቆና ገሮች በመቃወምና እርምት ለማድረግም በቼኮዝላቪያና በሃንጋሪ (ምስራቅ አውሮጳ) በሕዝቡ ሙከራዎች ቢደረጉም ሁለቱም ሙከራዎች በሶቭየት ታንኮች ድምጥማጣቸው ጠፍቷል።

ይኸው የዴሞክራሲ ዕንሰ ሃሳብ ቀውስ ማርክሲዝምን እያናጋው ራሳቸውን ሶሺያሊስትና ኮምኒስት እያሉ በሚጠሩት መካከል እንኳዋን ሰላም ሊገኝ አልተቻለም። መጀመሪያ ሶቭየት ሕብረትና ቻይና ተጣሉ፣ ቀጥሎ ዩጎዝላቪያና ሶቭየት ሕብረት ቀጥሎም ቻይናና ዩጎዝላቪያ ለጥቆም አልባንያና ሶቭየት ሕብረት፣ ተከትሎ ቻይናና አልባንያ በመጨረሻም ቻይናና ቬትናም ተዋጉ።

ይህንን የዴሞክራሲ ሕፀፅ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ለማስተካከል ገና ሶቭየት ሕብረት ከመስረትዋ በፊትና በሁዋላም ሙከራ ያደረጉ ጠበብቶችና አብዮታውያን ነበሩ። ሮዛ ልክስምበርግ፣ ካርል ካዊትስኪና ሌሎችም ሙከራዎች አድርገው ነበር። የፈየዳቸው ነገር ቢኖር አጓጉል ስም ተለጥፎባቸው - ለምሳሌ ካውትስኪን "መናፍቁ" ብለውታል- እንዳልባሌ ወደጎን መገፋታቸው ነው።

ከሁሉም በላይ የማርክሲዝም የግፍ ዕዋ በሶቭየት ሕብረት ሞልቶ የፈሰሰው ስታሊን ወደስልጣን ከመጣ በኋላ ነው። ትሮትስኪን የስልጣን ባላንጣው አድርጎ በማየቱም ከፓርቲውና ከተለያዩ ሃላፊነቶች ትሮትስኪን አነሳው፣ ያም አልበቃ ብሎ ካገሩ አባረረው። በዚሁ ሳይረካ ቅጥረኛ ነፈሰ ገዳዮችን አሰማርቶ በስደት በሚኖርበት አገር በሜክሲኮ በተኛበት በመጥረቢያ አስፈልጦ አስገደለው። "ታላቁ ሽብር" በሚባለው በዚህ ወቅት ስታሊን የፓርቲውንና የሰራዊቱን ከፍተኛ አመራር ያለምንም ሕጋዊ ምርመራና ፍርድ አስገደለ። ተከትሎም በአገሪተም ከፍተኛ ረሃብ ተከሰተ። ለማርክሲዝም ጥሩ ስሜት የነበራቸው የምዕራብ አውሮጳና የአሜሪካ የግራ ፓርቲዎችና ቡድኖች በስታሊን ግፍ ምክንያት ማርክሲዝምን እርም ብለው ሸሹት።

በተመሳሳይ በቻይና ከ1966-1976 አስር ያህል ዓመታት በወሰደው የ"ባሕል አብዮት" በተሰኘው ዕብደት በርካታ ምሁራን ያለምንም ሕጋዊ ፍርድ በ"ቀኝ መንገደኝነት" በመጠርጠራቸው ብቻ በአስከፊ የገጠር የጉልበት ስራ ሲማስኑ ብዙዎቹ ሕይወታቸው አለፈ። "ቀይ ዘብ" የተባሉ ተማሪዎችና ስራ አጥ ወጣቶች ዳኛም ከሳሽም ምስክርም እየሆኑ ለብዙዎች ሕይወት መጥፋትና መታሰር ምክንያት ሆኑ።

በ1970ዎቹ ማርክሲዝም ከአውሮጳ ማዕከሉ ወደ ሶስተኛ ዓለም ሲያመራ በእስያና በአፍሪካ ዘግናኝ ወንጀሎች በስሙ ተፈፀሙ። በካምቦዲያ (ካምፑቺያ) ፖል ፖት የተባለ ማርክሲስት የሚመራው የላባደር ፓርቲ ሁለት ሚሊዮን ያሕል ሕዝብ በጭፍጨፋ አለቀ። ከተሞችን ለቅቀን ወደገጠር እንገባለን፣ ገንዘብንም ከመገበያየት እናጠፋለን በሚል ዕብደት፣ መነፅር ያደረገውንና ማንበብ መፃፍ የሚችለውን ሁሉ በመፍጀት ተወዳዳሪነት የሌለው አረመኔነት ተፈፀመ። በኢትዮጵያም በቀይ ሽብር ወቅት በመንግስቱ ኃይለማርያም መሪነት የተፈፀመውን ግፍ እዚህ ላይ መጥቀሱ የግድ ነው።

ለማጠቃለል፣ ማርክሲዝም በ ላብ አደሩ አምባገነንነት ስም ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍሎች ለቅቆጣጠር ያደረገው ሙከራ መልሶ በራሱ ላይ ውርደትን አመጣበት። ነፃ ፍርድ ቤቶች አለመኖራቸው፣ ነፃ የሙያ ማኅበራት መቋቋም አለመፈቀዱ፣ ነፃ ፕሬስ አለመኖሩ፣ ወዘተ ማርክሲዝም መረን ለቆ ሲሄድ ተው የሚል ተቋም ሊገኝ ባለመቻሉ በጎርባቼቭ አማካይነት "ፔሮስትሮይካ" የተባለው እንቅስቃሴ ጮራ ፈነጠቀና እፎይታ ተፈጠረ።ይሁን እንጂ እንቅስቃሴው ማርክሲዝምንና ኮምኒዝምን ከውድቀቱ ሊያድነው አልቻለም።

ከዚያም ከ1989 ጀምሮ እስከ 1991 ባሉት ዓመታት ማርክሲዝምና ኮምኒዝም በአውሮጳ ተንኮታኩተው በመውደቅ የታሪክ ትቢያ ለመሆን በቁ:: ዛሬ አንዳንዶቹ ለምሳሌ ቻይናና ቬይትናም በስም እንጂ በተግባር ካፒታሊስት ናቸው:: እንደሰሜን ኮርያ ዓይነቶቹም የማርክሲዝምን አስከፊ ባሕርያት በታሪክ ሙዚየምነት እያስጎበኙ የውድቀት ጊዜያቸውን በመጠባበቅ ላይ ናቸው::

## ኢሕአፓና የማርክሲዝም ርዕዮተ ዓለም

ኢሕአፓ በማርክሳዊነቱ ዘመን (1975-1985) ርዕዮቱን የተጠቀመበት ባመዛኙ ባታጋይነት ሃይሉና በንድፈ ሃሳብ ትንተና መሳሪያነቱ ነው:: ፓርቲው ወደስልጣን ባለመምጣቱ ሌሎች ርዕዮትን የተቀበሉ መንግስቶች ከሰሩዋቸውና ከላይ ከተተነተኑት ስህተቶች ባመዛኙ ነፃ ነው ማለት ይቻላል:: ነገር ግን "ብቸኛ የላብ አደር ፓርቲ ነኝ" በሚል ማርክሳዊ አባዜ ከሌሎች ተመሳሳይ ፓርቲዎች ጋር ለነበረው የሻከረ ግንኙነት (ለምሳሌ ከመኢሶን ጋር) የተከተለው ማርክሳዊ ርዕዮት አስተዋፅኦ አላደረገም ማለት አይቻልም:: ቤላም በኩል የብሔሮችን ጥያቄ በሚመለከት ማርክሳዊ ቀኖናን መሰረት በማድረግ "የብሔሮችን የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል መብት" ማወቅ የሚለው አስተሳሰብ በፖሊሲው ላይ ብዥታን አልፈጠረበትም ማለትም ታሪክን መካድ ይሆናል::

የኢሕአፓን ዴሞክራሲ ተመክሮ መገምገም የሚቻለው ግን የፓርቲውን ውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲ ወደኋላ ዞሮ በማየት ነው:: ከሰራዊቱ የእርማት እንቅስቃሴ በፊት የነበሩ አናዳንድ ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑ አሰራሮችን የእርማት እንቅስቃሴ አካሂዶ ለማሻሻል ሞክሯል:: መዋቅሮችንንና ተቋሞችንም ምስርቷል:: በውስጡ የተነሱትን የልዩነት ሥታቄዎች ያስተናገደበት ሁኔታ ላይ ፍርድ ለመስጠት አስቸጋሪ ሁኔታዎች አሉ:: በከተማው ትግል ውስጣዊ ልዩነቱ በተነሳበት ወቅት ከደርግም ጋር ፓርቲው የሚፋለምበት ወቅት ስለነበረ ስለውስተ ፓርቲ ዴሞክራሲ ትክክለኛ ስዕል ማግኘት ያስቸግራል:: ፓርቲው ልዩነቶችን የማስተናገድ ፍላጎት ቢኖረው እንኳ ሁኔታው ሙሉ በሙሉ የሚፈቅድለት አልነበረም::

በገጠር እንደከተማው የወያነ ሃርነት ህዝብ ትግራይ የጦርነት አደጋና ውጊያ በውስጠ ፓርቲ ልዩነቶች አካሄድ ላይ ጥላውን አጥልቷል:: አንዳንድ በዴሞክራሲያዊ አካሄድ ሊጠቀሱ የሚገባቸው በጎ ክንዋኔዎች፤ ለምሳሌ የአባላት መብት አስጠባቂ ኮሚቴ መመስረትና ለታሰሩ ጓዶች ጥብቅና በመቆም ያደረገው አስተዋፅኦ በበጎ ጎኑ ሊነሳ ይገባል:: የተሰሩ ስህተቶች በዚህ ከለላ መታየት ይኖርባቸዋል::

ምናልባትም ከሁሉም በላይ ኢሕአፓ በማርክሳዊ ቅኝቱ ወቅት ካከናወናቸው ተግባሮች ሊኮራበት የሚገባ አባሎቹ ከተማሪነት ጊዜያቸው ጀምሮ እስከፓርቲ አባልነት ድረስ ያቀነቀኑለትና የተዋጉለት የ"መሬት ላራሹ" መፈክር ተግባራዊ መሆን ነው::

እንደሚታወቀው አዋጁ ከመታወጁ በፊት የመሬት ጥያቄ ከብሔረሰብ መብት ጥያቄም ጋር ተሳስሮ የደቡብና የምስራቅ ኢትዮጵያ ገበሬዎችና ዘላኖች በጭሰኝነት ባመዛኙ ከሰሜንና ከመሃል ኢትዮጵያ ለመጡ ባላባቶች የሚታሰሩበት ታሪካዊ ሁኔታ ነበር:: ይህ ጭቆና የኢኮኖሚና ባሕላዊ ዘርፎችን ይዞ በኢትዮጵያ ዜጎች መካከል ከፍተኛ ቅሬታን የፈጠረና መራራ ትግልን የወሰደ ጭቆና ነበር:: "መሬት ላራሹ" በማለት ተማሪው እሕአፓና ሌሎችም በወቅቱ የነበሩ ድርጅቶች ያነሱት መፈክር ባገሪቱ ባመዛኙ በአብዮቱ ምክንያትና ሃይል ተቀባይነት አግኝቶ፤ በመጨረሻም በመጋቢት 1975 እ. ኤ. አ. የመሬት አዋጅ በተራማጅነት መልኩ ሲታወጅና የኢትዮጵያን ገበሬና ዘላን ከዘላለም ባርነት ነፃ ለማውጣት ተችሏል:: ለዚህም አዎንታዊ ድርሻውን ኢሕአፓ ሊነሳ ይገባዋል::

ምንም እንኳ ፓርቲው በቋራ ሁለተኛ ጉባዔው ማርክሲዝምን መመሪያው ማድረጉን ማቆሙን ቢወስንም፤ አንዳንድ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ አሰራሮች ሙሉ በሙሉ ሳይቆሙ በቀጣይነት ስር ለመስደድ ችለዋል:: ከእነዚህም በተለይ በተወሰኑ

የአመራር አባላት በኩል የጋራ አሰራርን አለማክበር፣ ከድርጅቱ የአሰራር ሕግና ደንብ ውጭ መስራትና ተመሳሳይ ድርጊቶች መፈፀም መከሰትና እያደገ መምጣት ዋነኞቹ ተጠቃሾች ናቸው:: በነዚህም ምክንያቶች ድርጅቱ በጥቅምት 2007 መጨረሻ የተከፈለበት ሁኔታ ተከስቷል::

# ኢሕአፓና ሶሻል-ዴሞክራሲ

ኢሕአፓ ሶሻል-ዴሞክራሲን መመሪያው እንዲሆን በሶስተኛው ጉባዔ አንስቶ ቢወያይም በኦፊሴል ሶሻል-ዴሞክራሲን መመሪያው መሆኑን ያበሰረውና በጉዳዩም ላይ ሰፋ ያለ ትንተና ያደረገበትና በፅሁፍም ያወጣው በአራተኛው ጉባዔው በሰኔ 2006 ዓ. ም. ነው::

# ለምን ለውጥ አስፈለገ?

ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው ማርክሲዝም በገባው ቃልኪዳንና በተግባር ባሳየው ሁኔታ መካከል ታላቅ ክፍተት በመፈጠሩ በሕዝቦች ትግል ላይ ማነቆ ተፈጠረ:: በዚህም ምክንያት ድክመቶቹ በግላጭ በ1980ዎቹ መጨረሻ ገሃድ ሲወጡ ኢሕአፓም እንደአንድ ማርክሲስት ፓርቲ ይከተለው የነበረውን ርዕዮት መልሶ መመርመር ግድ ሆነበት:: በተለይም ማርክሲዝምን መላልሶ በመመርመር ርዕዮቱ በተለይ የመድበለ ፓርቲ አሰራርን ስለሚቀናቀንና መሰረታዊ የዴሞክራሲ መብቶችን ከመደብ አንፃር ብቻ ስለሚመለከት፣ ኢሕአፓ ለሚያደርገው ሕዝባዊ ትግል እንደማይመጥን ተረዳ:: ስለዚህም ባንድ በኩል በሺህዎች የሚቆጠሩ አባሎቹ የታገሉለትና የወደቁለት ክቡር ሰፊ ዓላማ እንዲቀጥል ለማድረግና በሌላ በኩል ደግሞ ዴሞክራሲያዊነትን የተላበሰ የትግል ርዕዮት መምረጥና መከተል አማራጭ የሌለው ወቅታዊ ጉዳይ በመሆኑ ኢሕአፓም ይህንኑ ለማሟላት በቃ:: እኒህን ጥንድ ዓላማዎች ያቀፈ ሆኖ የተገኘውም ሶሻል-ዴሞክራሲ ሆነ:: ሶሻል-ዴሞክራሲ፣ በ19ኛው መቶዎች ውስጥ ተመስርቶ በኮሚኒዝምና በካፒታሊዝም መካከል ለረጅም ጊዜ ከቆየ በኋላ በ1980ዎቹ የኮምኒዝም መውደቅ ምክንያት ሕይወት ዘርቶ ዛሬ የግራ ፓርቲዎች የሆኑ ሁሉ መመሪያቸው ያደረጉትም ነው:: ሶሻል-ዴሞክራሲ ባንድ በኩል የምዕራቡ ካፒታሊዝም ያመጣውን መሰረታዊና ዴሞክራሲያዊ የግለሰብ መብቶች ሲቀበል፣ በሌላ በኩል ደግሞ የድሆችን የአናሳ ቡድኖችን የሴቶችን የሰራተኞችን ወዘተ የቡድን ኢኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ መብቶች ይቀበላል፣ ለነዚህም ይታገላል:: በኢኮኖሚው መስክም ማርክሳዊና ኮምኒስታዊ የማዕከላዊ ዕቅድን/ዕዝን ፅንሰ-ሃሳብ አይቀበልም:: የገበያ ኢኮኖሚ የተባለውን ካፒታሊስታዊ ፅንሰ-ሃሳብ ተቀብሎ ነገር ግን በራሱ መንገድ በመቅረፅ የአፍቅሮተ ጭቁን ክፍሎች ፖሊሲ እንዲኖርም ይታገላል::

ዛሬ በዘመነ ግሎባላይዜሽን ግን ሶሻል-ዴሞክራሲ ክፉ ፈተና ገጥሞታል:: ባንድ በኩል በዓለም ገበያ ፊት ተፎካካሪ ለመሆን ሰራተኛን ማባረርና መቀነስ፣ ደምወዝና ጥቅማጥቅሞችን መቁረጥ ያስፈልጋል በሚሉ ክፍሎችና የሰርቶ አደሩን ቁጥር፣ የሰራ ፀባይና ጥቅሞች መቀነስ የለባቸውም በሚል ክርክር ውስጥ ይገኛል:: ሁለቱን በሚዛን አስገብቶ መሄድ መናገሩ እንጂ መተግበሩም ከብዶ ይታያል::

ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ይህንን መሆ ሲመርጥ ነጋዴዎችና የግል ባለሃብቶች በፕሮግራሙ እንደተመለከተው ያላቸውን አገር የመገንባት ምርብትና መዋዕለ ንዋያቸውን በኢኮኖሚ አውታሮች የማፈሰስ መብታቸውን ተቀብሎ ነው:: ይህም ሲሆን ፓርቲው በመንግስትና በባለፀጎች ሽሪክነት አፍቅሮት-ደሃ የሆነ ፖሊሲና አገርን በጋራ የመገንባት እንዲሁም ረሃብን ጨርሶ ከኢትዮጵያ ምድር የማጥፋት ዕቅዱን ማዕከላዊ አድርጎ ነው:: ሌሎችም የሃገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዚህ ዙሪያ ስምምነት እንዲፈጥሩ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) የበኩሉን የማያቋርጥ ጥረት ያደርጋል::

ከማርክሲዝም ያለያየው የርዕዮቱ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ሂደት በመሆኑ ዴሞክራሲያዊ አሰራርን ዋና መተክሉ አድርጎ በተለያዩ እርከኖች የሚገኙ አባሎቹ መሰረታዊ

እንዲጠበቅ ይታገላል። ይህም ልምዱ ከሕዝብ ጋር ለሚኖረው ግንኙነትና ከሌሎችም ፓርቲዎች ጋር ለሚኖረው ግንኙነት ዴሞክራሲያዊ መሆን ዋስትና ነው ብሎ ያምናል። በሶሻል-ዴሞክራሲ ላይ እንዲኖር ለሚፈለግ የበለጠ ግንዛቤ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) በዚህ ርዕስ ላይ ያዘጋጀውን ልዩ ፅሁፍ ማንበብ ይረዳል።

## BOOK REVIEW

**by**

***Sora Jarso***

**"Ethiopia: A View from Within"**
Michael B. Lentakis (2005), pp. 425
London, England: Janus Publishing Company

The author, Michael B. Lentakis is a Greek-Ethiopian born in 1932 in Addis Ababa who left Ethiopia for good in 1994 for Greece, his ancestral homeland. He narrates his first-hand life-long experience of a little over 60 years in Ethiopia. In the introduction, he strongly emphasizes that his book is different from others in that it is grounded on real lived experience, and uncharitably dismisses other Ethiopian books as hearsay and exaggerations.

In the following pages, I will summarize the main ideas contained in the book under these headings: The Contributions of the Greeks, the Italian invasion and the author's observations, the author's bias against the Ethiopian Revolution, his sexual openness, and finally major factual errors in the book.

1. The Contribution of the Greeks
Perhaps the greatest contribution of the book is that it documents very well the contributions of his family and himself in particular and the Greeks in general in the modernization of Ethiopia.

It is a historical subject that awaits detailed investigation along with the contributions of other communities in Ethiopia such as the Armenians to Ethiopia's modernity. The contributions started before the Italian invasion, continued through the invasion, and later as the young modernist Ethiopian state emerged from the ashes of war.

According to the author, in early 20th century, his father, Vasilios Lentakis together with 12 other young Greeks (from the island of Karpathos), decided to come to Ethiopia quitting their construction business in Egypt. The person instrumental in persuading them for the trip was another Greek who was Abyssinian honorary consul in Egypt, a Dr. Zervoudakis. He supplied them with a contract and an introduction letter to Emperor Menelik. Karpathians are reportedly the most renowned masons in Greece, and their art in chiseling, monument making, and stone and marble work is legendary. It seems, however, there was already a developed foreign community in Ethiopia going back to the days of Tewodros. In fact, during the arrival of the masons from Egypt, Dire Dawa, for example, had about 150 French inhabitants who were running a missionary school as well as the administration of the railway, and about 800 Greeks.

The author's father built the equestrian statue of Ras Mekonnen in Harer, and in recognition the highest honor, the Gold Medal, depicting the face of Emperor Haileselassie along with a certificate was bestowed upon him. Mr. Lentakis says that the Greeks asked Menelik to train Gurages (due to their industriousness) to do the basic stonework, especially chiseling, and to work in the quarries for the excavation of stone and marble, and the production of

asbestos lime. Menelik agreed and Gurages were brought from Wolisso, Wolkite, Endibir, etc.

According to the writer, the first Amharic newspaper was established by Andreas Kavadias under the name of Aemiro in 1911. The Asanides brothers built the first brick factory in Gulele, and until the 1950s they monopolized the market. They also established the first sawmills, in the forest of Managasha and in Ghinchi on the Ambo Road. The few doctors were mainly Greek, with some Germans. The only dentist, who mainly looked after the imperial court and the foreign community, was Constantinos Karakatsanis. He was the personal dentist of Emperor Haileselassie (or did the author mean Menelik?) and the godfather of his eldest daughter - Zauditu.

During the Italian invasion, many Greeks who were the majority of foreigners by far and who openly sympathized with the cause of Ethiopia had to leave the country. Some like the author's father served as army engineers in the Ethiopian army. Some Greeks, like Dr. Dasios, came as a volunteer with the Red Cross and reported to the world the bombing of the Red Cross field hospital for which he was imprisoned in a camp right up to liberation day.

After liberation, the Greeks embarked on an assortment of trade and business ventures including retail and wholesale trade of oilseeds, coffee, hides, and they established small soap, and oil factories and pharmacies. MOENCO and the A. Bess &Co. were among the biggest companies where Greeks played significant roles. The Greeks also formed one of the first football and basketball teams in the nation. While the Greek football had modest results, the basketball team dominated Ethiopian basketball competition by being a perennial power.

2. The Italian Invasion

According to the author, Italian colonization was openly racist. Ethiopians could not stay in Addis Abeba after 6 p.m. but had to be quatrtered in Mercato except for servants. When meeting an Italian, Ethiopians had to stand still and salute him respectfully. Cinemas were separate for Europeans and Ethiopians. Films showed to Ethiopians were mainly fascist propaganda.

Mussolini's plan was to make a home for at least 2 million Italiam immigrants, and use agrarain programs, such as "Ente Romagnia" and two others in the fertile lands of Ethiopia with an abundance of water. The numerous Greek half-castes in Ethiopia were openly persecuted and beaten in public. Many joined the patriots in Gojjam and Shewa; others went into exile.

Italian colonial policy was also implemented against foreigners. No foreigner was granted a government contract, or allowed to previous (privatize?) his profession. Vasili Aslanides had fled to Djibouti because he was wanted by the Italians for breaking the unjust arms embargo imposed by the Lerague of Ntaionsduring the Italo-Ethiopian war. He had imported arms from Yemen, Aden and Djibouti and built a small factory producing hand grenades, and had employed an Armenian, Nerses Nalbandian, to train Ethiopians in throwing these hand grenades at a training camp in Holeta. Both stayed in Djibouti until liberation. They were honored and decorated by the emperor after liberation for their services to the nation.

The author's father although under contract since Menelik's time was prohibited by the Italians from building any more. He was only allowed to operate a watermill that he constructed 50 meters from the Ras Mekonnen Bridge. His father had taken 10 years to complete constructing Menelik's mausolenium. The majestic church of Betemariam was constructed from huge stones weighing more than 1000 kilos each, well sculpted and are symmetrically joined. Eight granite lions were sculptured and stand on the veranda. In the undeground crypt, there are five tombs: one for Atse Menelik, one for Empress Taitu, one for Empress Zawditu, one for Abune Mattewos and the fifth for the youngest daughter of Haile selassie, Princess Tsehai. On top of the church, there is a huge stone crown. The golden crown of Menelik, Taitu, and Zawditu were molten to cover this stone crown, and the sun would always reflect off this splendid feature. According to the author, this stone crown is no longer there fot it was taken by the Russians during Mengistu's era as repayment for supplied weapons.

The author attributes to Ethiopia's luck for the assignment of General Orde Wingate as the commander of the British liberation forces. Wingate, according to the author, was one of the most unorthodox and controversial figures of the Second World War. He was liked neither by his superiors nor by his fellow officers. He was quarrelsome and eccentric. His superiors were glad to have him out of sight and to send him overseas as chief advisor to the emperor. Wingate soon became very friendly with the emperor, and completely gained his confidence. Wingate formed a force known as the “Gideon Force” and entered Ethiopia along with the emperor. Wingate helped the emperor to foil British schemes on Ethiopia by giving him cricial advice on moves he needed to make.

3. The author's distorted view on the Ethiopian Revolution

The author was a manager of a pharmaceutical company during the onset of the Ethiopian revolution, and hugely tied to the ancien regime. Leading members of the royal family owned parts of the companies he worked at and he was on first-name basis with most of them. It was therefore natural how he would react to the revolution that swept away that order. Besides, the author had a strong passion in hunting, and he was as familiar with Ethiopian hunting grounds as the palm of his hand, and hunted often with high officials. He says "there is no greater friendly bond existing in this world in my opinion than the friendship between hunters". He also narrates about the Ethiopian motor rally, a NASCAR equivalent that ran from 1964 until the revolution in 1974. Another *haute couture* activity was his narrative of the three bowling centers that has sprung up, one in Ghennet Hotel, another next to the Ethiopian Hilton, and the third and the largest-with ten lanes- on the road to the industrial area, the "rece". Italians, Greeks, and wealthy Ethiopians formed their own teams and enjoyed the party.

He mentions two Greeks who were commissioned to photograph the numerous archaeological sites and magificient landscape, fauna and flora, the beauty of various tribes to create posters and cards to promote tourism. He credits one Habteselassie Tafesse, minister of tourism under the emperor for creating the clever motto of "Thirteen Months of Sunshine".

The author tells the story of a shooting between a noted Oromo lawyer Assafa Doula whose clients included Europeans and their businesses and Jara Mesfin, Ras Mesfin's eldest son. Assafa was relentless in trying to collect illegally obtained rent deposit money by Ras Mesfin's daughter Mulu Mesfin. At the hotel, her husband, the tourism minister, pleaded with Assefa to drop the case, and Jara came over and made disparaging remarks about the lawyer. This started a shooting duel as a result of which both protagonists (Jara and Assefa) lost their lives.

Against this backdrop, it seems the writer could not appreciate the real causes of the Ethiopian revolution that gave rise to the event. He says the virus of anarchy introduced by the extreme leftist university students was reinforced by the jobless and criminal elements- and this from someone whose Ethiopian-born brother went back to Greece and was a famous student leader before he became a parliamentarian. He accuses Michael Imru as a "known leftist with Marxist ideas, and the son of a war hero".

To his credit, he admires the heroism of EPRP. Says he "surprisingly, opposition came from a Marxist party, the EHAPA, which enjoyed great support from students and young people; sponsored by the Chinese, it wanted a people's democratic communist government, and the army to withdraw to its barracks. They started a dynamic terrorist movement in the cities, especially in Addis Abeba, killing government officials, kebele members and army officers. The Derg branded them as "White Terrorists"". However, the author is very unflattering about Haile Fida...says "he was mostly responsible for killing Amharas...his weakness for drinking was what brought about his downfall". He cites a Greek mythology about Kronos, the father of gods who ate his own children because of his fear that one day they might challenge and overthrow him, to illustrate how the Ethiopian revolution ate its own children.

****************************


**ለምትፅፉልን ወይም ለምትደውሉልን አድራሻችን**

**EPRP (Democratic)**
**850 Sligo Avenue Suite # 8**
**Silver Spring MD 20877**

**EPRP (Democratic)**
**P. O .Box 88675**
**Los Angeles CA 90009**

**EPRP (Democratic)**
**P. O. Box 8141**
**Silver Spring MD 20910E**

**mail: Emailtoeprp@aol.com**

**Telephone:- 301-578-4466**
**301-578-4465**
**Fax: 202-449-8363**



ዐቢዮት